# በኖርዝ ኢስት

# ነጻነትን ማወጅ



በዩናይትድ
ኪንግደም
ለዲሞክራሲና
ለሲቪል መብቶች
የተደረገው ትግል
በዚህ አካባቢ
ነዋሪዎች ላይ በጎ
ተጽዕኖ ያሳደረው
እንዴት ነው?

## ሕይወትና ነጻነት

## ከቴኪንግ ሊበርቲ ፕሮጀክት

## የተገኙ የምሥክርነት ቃሎች

heritage lottery fund
LOTTERY FUNDED

Turn a new page

Newcastle Libraries

Newcastle
City Council

# በኖርዝ ኢስት

# ነጻነትን ማወጅ

**ነጻነትን ማወጅ (ቴኪንግ ሊበርቲስ) የተባለው ፕሮጀክት ከHeritage Lottery በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እኤአ ከኅዳር 24 ቀን 2010 አንስቶ እስከ ጥር 30 ቀን 2011 ድረስ በኒውካስል ከተማ ቤተ መጻሕፍት በኖርዝ ኢስት ነጻነትን ማወጅ በሚል ርዕስ ክፍት ሆኖ የቆየው አውደ ራእይ ቀጣይ ውጤት እንዲኖረው ለማድረግ የታቀደ ነው።**

ከብሪቲሽ ቤተ መጻሕፍት (British Library) ጋር በመተባበር የቀረበው አውደ ራእይ ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ለዲሞክራሲ በተደረገው የ900 ዓመት ትግል ላይ ያተኮረ ሲሆን በተለይ ደግሞ ትግሉ በኖርዝ ኢስት ለሲቪል መብቶችና ለዲሞክራሲ በተደረገው ትግል ውስጥ የነበረውን አስተዋጽኦ አጽዕኖት ሰጥቶ ያሳየ ነው። ከተማው ከፓርላማው

ቤተ-መዘክር በውሰት ያገኘውን ሪፕረዘንቴሽን ኦፍ ፒፕልስ አክት የተባለውን የ1832 ደንብ ያቀረበ ሲሆን የትግል መፈክሮችን፣ ተቃውሞዎችን፣ እሴቶችን፣ መብቶችን፣ ነጻነቶችን እንዲሁም ብሪታንያዊ መሆን ምን ማለት ነው የሚለውን ጉዳይ በጥልቀት የዳሰሰ ነው።

በአውደ ራእይው ውስጥ ጎብኚዎች ነጻነትን ማወጅ በተባለው ፕሮጀክት ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ግለሰቦች የግል ታሪክ የማየትና የመስማት አጋጣሚ አግኝተው ነበር። ይህ በHeritage Lottery የገንዘብ ድጋፍ የተካሄደ ፕሮጀክት ከተለያዩ አገሮች የመጡ ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች በብሪታንያ ስለተካሄደው የመብቶችና የሲቭል ነጻነት የትግል ታሪክ ብዙ ነገር እንዲገነዘቡ ረድቷቸዋል። የቡድኑ አባላት በተከታታይ በተካሄዱ አውደ ጥናቶች ላይ መገኘታቸው የሰብዓዊ መብት ዝርዝር ጉዳችንና እሴቶችን በጥልቀት ለመመርመርና ወደ ዩናይትድ ኪንግደም ያደረጉትን ጉዞ በተመለከተ አንዳቸው ስለ ሌላው ለማወቅ አስችሏቸዋል።

እነዚህ ዓውደ ጥናቶች ሲካሄዱ በየአገሮቻቸው ያሳለፉትን የራሳቸውን ተሞክሮ መለስ ብለው በመመልከት በኖርዝ ኢስት ለመኖር የበቁት እንዴት እንደሆነ ታሪካቸውን ለሌሎች አጋርተዋል። ስላጋጠማቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲሁም ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ መኖር ሲጀምሩ ቢሮክራሲው ምን ያህል ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነባቸው ተርከዋል። የእነዚህ ሰዎች ዘገባዎች ግዙፍ ከሆነው የአውደ ራእይው ግብዓት በተጨማሪ ጠቃሚ የሆነ ዘመናዊ መረጃ ሆኖ በመገኘቱ  በጽሑፍ እንዲቀመጥ የማድረጉ ጠቀሜታ ታምኖበታል።

ብዙ ሰዎች ስለ እነዚህ ባሕላዊ ጠቀሜታ ያላቸው ታሪኮች እንዲያውቁ ለማድረግ ሲባልም በአካባቢው የሚኖሩትን ጥገኝነት ጠያቂዎች፣ ስደተኞችና ከሌላ አገር የመጡ ሠራተኞች ትረካ በማሰባሰብ ምስክርነታቸውን በብዙሐኑ ዘንድ ለንባብ ለማብቃት ተወስኗል። አሁን እያነበቡት ያለው ፓምፍሌት ሊዘጋጅ የበቃው በዚህ መንገድ ነው።

የምሥክርነት ቃሉን በአብዛኛው የሰጡት በአካባቢው የሚገኙ የESOL ተማሪዎች ናቸው። ጽሑፎቻቸውን አስተዋጽኦ ያደረጉት ተማሪዎች ከቻይና፣ ከሆንግ ኮንግ፣ ከኢራን፣ ከቱርክ፣ ከፖላንድ እና ከሕንድ የመጡ ናቸው። የእነርሱ ታሪክ የጥገኝነት ጠያቂዎችን፣ ከሌላ አገር የመጡ ሠራተኞችንና ስደተኞችን ሁኔታ በተሻለ መንገድ ለመረዳት እንዲሁም እነዚህ ቡድኖች በአካባቢው የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ጉልህ ድርሻ አጉልቶ ለማሳየት ይረዳል ብለን እናምናለን።

www.newcastle.gov.uk/libraries



## ናሰራ (ባንግላዴሽ)

መጻፍ የፈለግሁት አባቴ ወደ እንግሊዝ ስለመጣበት ሁኔታ ነው። አባቴ ወደ እንግሊዝ የመጣው ከስልሳ ዓመት በፊት ነው። እንግሊዝ ውስጥ ለረጅም ጊዜ ኖሯል።

መጀመሪያ ላይ ይኖር የነበረው ለንደን ውስጥ ነው። ፋብሪካ ውስጥ ተቀጥሮ ይሠራ ነበር። ብዙ ገንዘብም ያገኝ ነበር። ባንግላዴሽ ውስጥ ሥራ አልነበረውም፣ ምክንያቱም ባንግላዴሽ ምንም ገንዘብ አልነበራትም።

አባቴ በመጀመሪያ ወደዚህ እንደመጣ ታላቅ ወንድሜ አብሮት እንዲሆን ማመልከቻ አስገብቶ ነበር። ተሳካለት።

አባቴ ሁለተኛ ጊዜ ወደዚህ ሲመጣ ከወንድሜ ጋር በሌችስተር ይኖሩ ነበር። እኔና ቤተሰቤ አብረነው እንድንኖር ማመልከቻ አስገብቶ ተቀባይነት አገኘ። አሁን አባቴ በሕይወት የለም።

ስሜ ናሴራ ይባላል። የመጣሁት ከባንግላዴሽ ነው። ወደ እንግሊዝ ከመጣሁ 10 ዓመት ሆኖኛል። ወደ እንግሊዝ የመጣሁት ከአባቴ ጋር ነው። መጀመሪያ ላይ ሌችስተር ውስጥ ሦስት ዓመት ኖርኩ። አሁን ኒውካስል ውስጥ መኖር ከጀመርኩ ሰባት ዓመት ሆኖኛል። ነጻ በመሆኔ ደስተኛ ነኝ።

## ስማቸው ያልተጠቀሰ (ቱርክ)

ልጅ እያለሁ ትልቅ ችግር ነበረብኝ። ቱርኮች ስለነበሩ ብቻ ለእኔ ወገን ጥላቻ ያላቸው መምህራን ያሉበት ትምህርት ቤት ገባሁ።

በቱርክ ምሥራቃዊ ክፍል ነው የኖርኩት። አንዳንዶቹ ኩርዲሽ አንዳንዶቹ ደግሞ ቱርኮች ነበሩ። የእኔ ከተማ እና አካባቢው በሙሉ የኩርዲሾች ሲሆን በአካባቢው የሚነገረውም የኩርዲሽ ቋንቋ ነው። የእኛ ሃይማኖታዊ ቡድንም ሆነ የምናምንበት ሃይማኖታዊ ቀኖና የተለየ ነው። መስጊድ አንሄድም ወይም ሙስሊም ሴቶች የሚለብሱትን መሸፈኛ (ሂጃብ) አንለብስም። ይሁንና ትምህርት ቤት ስገባ መምህራኑ ስለሚቆጡ በሚል የቀሩት የእኔ ወገኖች ኩርዲሽ አይናገሩም ነበር።

አንዳንድ ጊዜ መምህራችን ልጆቹ በኩርዲሽ ቋንቋ ሲነጋገሩ ያገኟቸዋል። ከክፍል ውጪ በኩርዲሽ የሚያወሩ ተማሪዎች ካሉ ሄደን እንድንነግራቸው ይነግሩን ነበር። ጨርሶ በኩርዲሽ እንድናወራ ስለማይፈለግ በዚያ ፋንታ ተርኪሽ እንድንማር ተደረገ። መንግሥት ትምህርት ቤቱን ሳይዘጋው በፊት 5ኛ ክፍል ድረስ ተማርኩ። ከዚያ በኋላ ግን ትምህርት ቤቱ ወደ ወታደሮች ማረፊያነት ተቀየረ።

አገሬ ውስጥ ብዙ ችግር ስለነበረብኝ ወደ እንግሊዝ የመጣሁት በፖለቲካ ምክንያት ነው። እንግሊዝ ውስጥ ሰብዓዊ መብት ይከበራል። እዚህ የምኖረው ከቤተሰቤ ጋር ሲሆን በጣም ደስተኛ ነኝ። እንግሊዝ ለእኔም ሆነ ለቤተሰቤ ደህንነት አስተማማኝ ቦታ ነው።

## ፋህሚዳ (ባንግላዴሽ)

መጻፍ የፈለግሁት ስለ ነጻነት ነው። እናቴ እንደነገረችን ከሆነ እኔ አገር ከረጅም ጊዜ በፊት ሴቶች ጉርድ ሸሚዝ እንዲለብሱ አይፈቀድላቸውም ነበር። አሁን ሁኔታዎች ተለውጠዋል፤ ሰዎችም ነጻነት አላቸው።

ትዳር ስይዝ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም መጣሁ። የኖርኩት አማቴ ቤት ነው። እንግሊዝኛ መናገር እንደማልችል ታውቅ ነበር። በዚህ ምክንያት አማቴ እንግሊዝኛ መማር እንደሚያስፈልገኝ በመግለጽ እናንተ [ESOL] አነጋገረችልኝ። የESOL ትምህርት እንድጀምርም ማመልከቻ አስገባችልኝ።

ባለቤቴ ብዙ ነጻነት ሰጥቶኛል። ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ መኪና መንዳት ተምሬአለሁ። ቤቴ ውስጥ ሆኜ ልብስ እየሰፋሁ ቀሚስ፣ ቡርካሃስ እና ሸሚዝ እሠራለሁ። ቤተሰቤ በዚህ አገር ያገኘው ነጻነት በጣም ሰፊ ነው። በመምህሬ ጆአን በጣም ደስተኛ ነኝ። በጣም ደግ እና ሰው መርዳት የምትፈልግ እንዲሁም ወዳጃዊ ሰው ናት።

### ዓውደ ጥናቱ በተካሄደበት ወቅት



## ጁስና (ባንግላዴሽ)

አባቴ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የመጣው ባንግላዴሽ ውስጥ ድሃ ስለነበረ ነው። አገራችን በጣም ደሃ የነበረች ሲሆን ብዙ የሰብዓዊ መብት ረገጣም ነበር። እኔ አልደረስኩበትም። ይሁንና አባቴ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የመጣበት ምክንያት ይህ እንደሆነ ሲናገር ሰምቻለሁ። አባቴ በጣም እምነት የሚጣልበት ሰው ነው። አገራችን ነጻ አይደለችም፤ ሆኖም ነጻነት ጥሩ ነገር እንደሆነ አምናለሁ። አባቴ ቤተሰቡን ደግፏል።

## ስማቸው ያተጠቀሰ (ሆንግ ኮንግ)

የምጽፈው ስለ አገሬ ስለ ሆንግ ኮንግ ነው። ሆንግ ኮንግ በጣም ሰላማዊና ውብ ቦታ ናት። ናሙና የሚሆኑ የብዙ አገሮችን የተለያዩ ሕንጻዎችንና ሬስቶራንቶችን ይዛለች። ብዙ የተለያዩ ሰዎች ሆንግ ኮንግ ውስጥ ይሠራሉም ይኖራሉም። ነጻ አገር ነበረች።

እኔ ወደዚህ የመጣሁት ከባለቤቴ ጋር ነው። የእርሱ ቤተሰቦች ለኑሮ ወደ እንግሊዝ የመጡት ከረጅም ጊዜ በፊት ነው። በዚያ ጊዜ ከቻይና ለሚመጡ ሰዎች በዚህ መኖር በጣም አስቸጋሪ ነበር። እንግሊዞች ቻይናዎችን አይወዷቸውም ነበር። አንዳንድ እንግሊዛውያን ከቻይናዎች ጋር ይጣሉ ነበር። ቻይናዎቹ ጠንክረው ይሠሩ ነበር። ከረጅም ጊዜ በፊት ቻይናዎች እንግሊዝኛ መናገር አይችሉም ነበር።

ዛሬ አብዛኛዎቹ እንግሊዛውያን ቻይናዎችን ይወዷቸዋል፤ ምክንያቱም አብዛኛዎቹ እንግሊዝኛ መናገር ይችላሉ። አብረው ያወራሉ፤ አብረው ይሠራሉ።

ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ነጻነት አለ፤ እንዲሁም በጣም ሰላማዊ አገር ነው። በየዓመቱ በምርጫዎች መካፈልና ለሰዎች ድምጽ በመስጠት ትክክለኛውን ነገር ማድረግ ትችላለህ።

በዓውደ ጥናቱ ላይ የሕይወት ታሪኮቻቸውን ሲወያዩ



## ስማቸው ያልተጠቀሰ (ቻይና)

ይህን ደብዳቤ የምጽፈው በአገሬ ውስጥ ያለውን አፈና በተመለከተ ነው።

እኤአ በ1989 በዋና ከተማዋ ቤጂንግ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በይፋ የሚፈጸመውን ጉቦና ሙስና በተመለከተ መንግሥትን ለመቃወም የተቃውሞ ሰልፍ አደራጅተው ነበር። በጥቂት ቀናት ጊዜ ውስጥ ይህ እንቅስቃሴ ወደ ሁሉም ብሔራዊ ዩኒቨርሲቲዎች ተዛመተ። መንግሥት የተማሪዎቹን ዓመጽ ለመቆጣጠር ሠራዊቱን ላከ። እነርሱም ተኩስ በመክፈት አንዳንድ ተማሪዎችን ገደሉ። ይህ እውነተኛ ታሪክ ነው።

## ስማቸው ያልተጠቀሰ (ባንግላዴሽ)

መጀመሪያ ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የመጡት የባለቤቴ አባት ናቸው። ኑሯቸው ለንደን ውስጥ ነበር። ሬስቶራንት ውስጥ ተቀጥረው ይሠሩ ነበር። ከዚያ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ባለቤቴ ወደ ለንደን መጣ። ባለቤቴ ለንደን ውስጥ 10 ዓመት ኖሯል። ወደ ኒውካስል የመጣው ከ21 ዓመት በፊት ነው። ከዚያ ወደ ባንግላዴሽ ተመለሰ። ከዚያም እኤአ በ1995 ከእኔ ጋር ተጋባንና እኤአ በ1996 ወደ ኒውካስል መጣሁ። ከባለቤቴ ቤተሰቦች ጋር ለ6 ዓመት ያህል የቆየሁ ሲሆን ከዚያ በኋላ ሌላ ቤት ቀየርኩ። አሁን እኔ፣ ባለቤቴና ልጆቻችን የራሳችን ቤት ውስጥ እንኖራለን።

ከ6 ዓመታት በፊት ነጻነት አልነበረኝም። አሁን ብዙ ነጻነት አለኝ። ባለቤቴ በጣም ጥሩ ሰው ነው። ሥራ መሥራት እንደምችል፣ ወደ ስፖርት ማዕከል ሄጄ ስፖርት መሥራት እንደምችልና እንግሊዝኛ መማር እንደምችል ይነግረኛል።

እንግሊዝኛ መማሬ ለእኔ ጥሩ ነው። እራሴን ችዬ እንቀሳቀሳለሁ። አልፈራም።

## ስማቸው ያልተጠቀሰ (ፖላንድ)

የመጣሁት ከፖላንድ ነው። ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የመጣሁበት ምክንያት አገሬ ውስጥ ሥራ ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ስለሆነ ነው። እዚህ ከመጣሁ 4 ዓመት ሆኖኛል። የመጀመሪያ ሥራዬን ያገኘሁት ወደ ዩናይትድ ኪንግደም ከመጣሁ በኋላ ነጻ አገልግሎት ስሰጥ ቆይቼ ነው። አሁንም ገና እንግሊዝኛ እየተማርኩ ስለሆነ ያገኘሁት ሥራ የከፊል ጊዜ ብቻ ነው። የመንጃ ፈቃድ ለማውጣት የመንጃ ፈቃድ ፈተናውንም ማለፍ አለብኝ። ይህ ደግሞ የተሻለ ሥራ እንዳገኝ ይረዳኛል።

አገሬ ውስጥ ከነበረኝ ይልቅ እዚህ ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ እውነተኛ ነጻነት ይሰማኛል። ለምን? ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ምንክያቱ አንድና አንድ ነው - ሥራ ማግኘቱ።

## ፓሪሳ (ኢራን)

ፓሪሳ እባላለሁ:: ትውልዴ ኢራን ነው:: መጻፍ የፈለግሁት አገሬ ውስጥ ያለውን የሲቪል ነጻነት በሚመለከት ነው:: ኢራን ውስጥ የሴቶች መብት በጣም የተገደበ ነው:: ሴቶች ድምቅ ያሉ እንደ ቀይ፣ አረንጓዴ ወዘተ ያሉ ቀለማትን ለልብስነት መጠቀም አይችሉም:: ሥራ በሚሠሩበት ጊዜም ሆነ ውጭ በሚወጡበት ጊዜ ሳይቀር ሂጃብ መልበስ ይጠበቅባቸዋል:: አለባበሳችሁ እንደሚጠበቀው ዓይነት ሆኖ ካልተገኘ እሥር ቤት ልትወርዱ ወይም ቅጣት ሊጣልባችሁ ይችላል::

ኢራን ውስጥ በሳይኮሎጂ ትምህርት ዲግሪዬን አግኝቻለሁ:: ትምህርቴን ጨርሼ ሥራ ለማግኘት 2 ዓመት ሙሉ ደክሜአለሁ:: በመጨረሻ አንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ሥራ አገኘሁ:: ሁለት የቃል ፈተናዎችን ካለፍኩ በኋላ ስለ እኔና ስለ ቤተሰቤ በጥልቀት የሚያጣራ ሰው ተላከ:: ከነበረኝ ብቃት ይልቅ የላቀ ቦታ የሚሰጠው ነገር ይህ ነበር::

ስለ ሃይማኖት፣ መንግሥትን በሚመለከት ስላለኝ አቋምና ወደ ሥራ ወይም ወደ ውጭ ስወጣ ስለሚኖረኝ አለባበስ ተደጋጋሚ ቃለ መጠይቅ ተደረገልኝ:: ትምህርት ቤት ውስጥ ለመሥራት ሦስት ልብስ መደራረብና እጆቼን ሳይቀር መሸፈን ይጠበቅብኝ ነበር:: ይህ በጣም ከባድ ነበር፤ ምክንያቱም ሰውነቴን እንኳን እንደ ልብ ማንቀሳቀስ አልችልም:: ደሞዜ በጣም አነስተኛ ነበር:: በዚህ ሁኔታ ከአንድ ዓመት በላይ መዝለቅ አልቻልኩም::

ኢራን ውስጥ ሰዎች የራሳቸውን ልብስ፣ የሚኳኳሉበትን መንገድም ሆነ የፀጉር አሠራራቸውን በተመለከተ እንኳን መብት የላቸውም:: እነዚህ እንግዲህ በጣም መሠረታዊ የሆኑ የሰው ልጅ መብቶች ናቸው:: ይሁንና በሌሎች አገሮች ያሉ ሰዎች እነዚህን ተራ መብቶች የሚነጥቃቸው ስለሌለ የራሳቸውን ልብስ መምረጥ ይችላሉ::

### የቴኪንግ ሊበርቲስ ቡድን



# ኡቤይዳ (ባንግላዴሽ)

የባለቤቴ አባት ወደ እንግሊዝ የመጡት ከስልሳ ዓመታት በፊት ነው። የሚኖሩት ብራድፎርድ ውስጥ ነበር። ሥራቸው ፋብሪካ ውስጥ ነበር። አሁን ጡረታ ወጥተዋል። ባለቤቴ ደግሞ ወደ እንግሊዝ የመጣው ከሰላሳ ዓመታት በፊት ነው። ሬስቶራንት ውስጥ ይሠራ ነበር። አሁን ግን ታክሲ ይዟል።

እኔ አገር ሕጉ ጥሩ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በጣም አስቸጋሪ ይሆናል። አንዳንድ ሰዎች ሕጉን ተከትለው መኖር ይችላሉ። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ስለ ሕጉ ግድ አይሰጣቸውም። ቀደም ሲል እኔ አገር ወንጀል በጣም የተስፋፋ ነበር። አሁን የዚያን ያህል አይደለም።

እንግሊዝ ውስጥ የሕግ አተገባበሩ በጣም ያስደስታል። እንግሊዝ ውስጥ ሁሉም ነገር ጊዜውን ጠብቆ ይከናወናል። መንግሥት ሁሉንም ሰው የሚይዘው በአክብሮት ነው። እዚህ አገር አፈናና ስርቆት እምብዛም አይታይም። እኔ አገር አፈናና ስርቆት እንዲሁም ግድያ በጣም የተስፋፉ ነገሮች ነበሩ። አሁን ግን እንደዚያ አይደለም።

ባለቤቴ ጥሩ ሰው ነው። ስወጣ ብዙ ነጻነት አለኝ። ባሌ ችግር አይፈጥርብኝም። ነጻነት ያለበት ሕይወት ደስ ይለኛል። ነጻነት የሌለው ሕይወት አልወድም።

## በኒው ካስል ቤታችን



## ካሊድ (ኢራን)

ወደ ዩናይትድ ኪንግደም የመጣሁት ከሰባት ዓመት በፊት ወደ ዩናይትድ ኪንግደም በመጣሁባቸው የመጀመሪያዎቹ ሦስት ወራት የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤቱ ቀደም ሲል በነበርኩበት አገር ማለትም በጀርመን የእጅ አሻራዬን አገኘ። የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤቱ ወደ ጀርመን መመለስ እንዳለብኝ ውሳኔ ላይ ደረሰ። የነበርኩት ለንደን ውስጥ በሚገኝ የኢሚግሬሽን ሆስቴል ውስጥ ስለነበር ፖሊስ ያለ ችግር ወደ ጀርመን እንዲያዘዋውረኝ ከሆስቴሉ መውጣት ነበረብኝ።

ወደ ጀርመን እንዳይመልሱኝ ምን ማድረግ እንደምችል ወይም ምን ማድረግ እንደማልችል ምንም የማውቀው ነገር አልነበረም።

ይሁንና ዩናይትድ ኪንግደም ውስጥ ለመቆየት ቆርጬ ነበር። ከባዱ ነገር የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤቱን ውሳኔ ማስለወጥ ነበር። ለእኔ በጣም ከባድ ነበር - ምናልባትም በሕይወቴ ውስጥ ካጋጠሙኝ በጣም አስቸጋሪ ነገሮች ሁሉ የከፋ። ታዲያ ምን ማድረግ እችላለሁ?

የኢሚግሬሽን መኮንኑ ወደ አየር ማረፊያው ሲወስደኝ ተረጋግቼ ነበር። ብዙም አልተረበሽኩም። ኤርፖርት እንደደረሰን በነበሩት የመጀመሪያ ጥቂት ደቂቃዎች በእኔ ምክንያት አየር ማረፊያው በፖሊስና በኢሚግሬሽን ሠራተኞች ተሞላ።

- መስታወት በመስበር እጆቼን እና ደረቴን እንዲሁም ሆዴን በስባሪው ቆረጥኩ። ከዚያም ፖሊሱን አንድ እርምጃ ከተጠጋኝ በጠርሙስ ስባሪው አንገቴን እንደምቆርጥ ነገርኩት። አጠገቤ የነበረው አስተርጓሚው ብቻ ነበር።

የመስታወት ስባሪውን አንገቴ ላይ አድርጌ ለጥቂት ሰዓታት ከቆየሁ በኋላ ከኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤቱ ድርጊቴን ካቆምኩ እንማይልኩኝ የሚገልጽ ፋክስ ስለተላከ እሺ ብዬ እጄን ሰጠሁ።

ከጥቂት ዓመታት በፊት ከጓደኞቼ አንዱ የሆነው ቴሃ፣ የሆም ኦፊሱን ውሳኔ ሲጠብቅ አምስት ዓመት ቆይቶ ነበር። ላለፉት አምስት ዓመታት ሲጠብቅ ቢቆይም ምንም ምላሽ ስላላገኘ በጣም ተበሳጭቶና አዝኖ ነበር።

አንድ ቀን ከእንቅልፉ ሲነቃ የዛፍ ቁራጭ ያዘና ወደ ፖሊስ ጣቢያው በመሄድ የፊት ለፊቱን በር መስታወት መሰባበር ጀመረ። ከዚያም ፖሊሶቹ በቁጥጥር ሥር አውለው ለምን መስኮቱንና በሩን እንደሰባበረ ጠየቁት። እርሱም "የኢሚግሬሽን መሥሪያ ቤቱን ውሳኔ በመጠበቅ ብዙ ዓመት ባሳልፍም ምንም ዓይነት ምላሽ አላገኘሁም። ከባለቤቴና ከቤተሰቤ ተለያቼ 5 ዓመት ሙሉ ጠበቅሁ፤ የኢሚግሬሽን ቢሮው ግን አሁንም ገና ያስጠብቀኛል። በነገረ ፈጅ እንዲሁም በአካባቢው የፓርላማ አባል በኩል ምላሽ ለማግኘት ሞከርኩ፤ ሆኖም ምንም ዓይነት ውሳኔ ላገኝ አልቻልኩም። በጣም ስለተናደድኩና ከዚህ በላይ መጠበቅ ስለማልችል ፖሊስ አንድ ነገር እንዲያደርግ ስል ነው" በማለት መለሰላቸው።

## ፓዎል (ሕንድ)

ፓዎል ፓቴል እባላለሁ፡፡ ጉጅራቲ የሚባለው የሕንድ ግዛት ተወላጅ ነኝ፡፡ መጻፍ የፈለግሁት ስለ አገሬ ማለትም ስለ ዲሞክራሲው፣ ስለ አስተዳደር ሥርዓቱ፣ ስለ ሰብዓዊ መብት ጥሰት እንዲሁም ሕግና ደንብ ስለመተላለፍ ነው፡፡

እኔ አገር ሕግ የሚተላለፉ ሰዎች ይቀጣሉ፡፡ አገሪቱ አልኮል ጠጥቶ መኪና ማሽከርከርን የሚከለክለውን ደንብ የመሳሰሉ ብዙ ዓይነት ደንቦች አሏት፡፡ አልኮል ለመሸጥ ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል እንጂ ማንኛውም ሰው መሸጥ አይችልም፡፡ አልኮል ደብቀው የሚገኙ ወይም በድብቅ የሚሠሩ ሰዎች ይቀጣሉ እንዲሁም ሊታሠሩ ይችላሉ፡፡ ፖሊስ በቁጥጥር ሥራ ያውላቸውና ለመንግሥት ቅጣት እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ ፍርድ ቤቱም (የ3 ወር ወይም የ6 ወር) የእስር ቅጣት ሊበይንባቸው ይችላል፡፡

ሕግ የሚተላለፉ ብዙ ዓይነት ሰዎች አሉ፡፡ አውቶብሶች ላይ መብላት ወይም መጠጣት ወይም ሲጋራ ማጨስ አይፈቀድም፤ ሆኖም አንዳንድ ጊዜ ፖሊሶቹ ዝም ስለሚሉ ያጨሳሉ፡፡ አንዳንድ የመንግሥት ፖሊሶች ሰዎች እንደዚያ እንዲያደርጉ ለመፍቀድ ገንዘብ ይቀበላሉ፤ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ መጥፎ ነገር ያስደስታቸዋል፡፡ ደሃ አይወዱም፡፡

ሕንድ ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ አንድ አውቶብስ ላይ ተሳፈርኩ፡፡ አውቶብሱ በሰው ስለተጨናነቀ ሰዎቹ መቀመጫ አጥተው ቆመዋል፡፡ ጸያፍ ንግግር የሚናገር አንድ መጥፎ ሰው ተሳፍሮ ነበር፡፡ በጣም አበሳጭቶኝ ስለነበር ለተቆጣጣሪው ተናገርኩበት፡፡ በዚህ ጊዜ እኔንም ያጋጠመኝ ጥሩ ነገር አልነበረም፡፡ ሰውዬው ከእኔ ጋር መጨቃጨቅና እኔ ላይ መጮኽ ጀመረ፡፡ የሚገርም ሰው ነው፡፡


### ምሥጋና

የኒው ካስል የከተማ ቤተ-መጻሕፍት (Newcastle City Library) አገልግሎት ጆአን ፓቲሰን (Joan Pattison) እና ክሪስ ቴይለር (Chris Taylor) ከSuperkrush Films ላበረከተቱ ከፍተኛ እገዛ ልባዊ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡

ከሁሉም በላይ የምሥክርነት ቃላቸው በዚህ ጽሑፍ ገጾች ላይ ለንባብ እንዲበቃ የፈቀዱትን ሁሉ ልናመሰግናቸው እንወዳለን፡፡ ያለ እነርሱ ትብብር የዚህ ቡክሌት ሕትመት እውን ሊሆን አይችልም ነበር፡፡



**ለተጨማሪ መረጃ የሚከተለውን የድረ-ገጽ አድራሻ ይመልከቱ፦**
**www.newcastle.gov.uk/libraries**

**አድራሻ**
City Library, Charles Avison Building, 33 New Bridge Street West
Newcastle upon Tyne NE1 8AX.

**ስልክ፦ 0191 277 4100**
ኢ-ሜል፦ information@newcastle.gov.uk